የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ — ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 1
ADDIS ABABA – 24th October, 1996


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
ለመጠጥ ውሀ ልማትና መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ........................ ገጽ ፪፻፷፬


## CONTENTS


Proclamation No. 46/1996
International Development Association Loan Agreement for Financing the Water Supply Development and Rehabilitation Project Ratification Proclamation ........................ Page 264


### አዋጅ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፹፱

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለመጠጥ ውሀ ልማትና መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር. ፳፬ ሚሊዮን (ሃያ አራት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር.) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፮ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለመጠጥ ውሀ ልማትና መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 46/1996

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of twenty four million Special Drawing Rights (SDR 24,000,000) for financing the Water Supply Development and Rehabilitation Project, was signed in Washington D.C., on the 15th day of May, 1996;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 24th day of October, 1996;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

*1. Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Financing the Water Supply Development and Rehabilitation Project Ratification Proclamation No. 46/1996."


ያንዱ ዋጋ / Unit Price } 1·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ሜይ ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፮ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፪ሺህ ፰፻፵፪ ኢ.ት. የብድር ስምምነት ነው ።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳፬ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር. /ሃያ አራት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር./ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 2842 ET signed in Washington D.C. on the 15th day of May, 1996 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. Power of the Minister of Finance

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of twenty four million Special Drawing Rights (SDR 24,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of October, 1996.

Done at Addis Ababa, this 24th day of October, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
Berhanena Selam Printing Interprise